# በቅንጅት ማኒፌስቶ ውስጥ ከተካተቱት ሃሳቦች ጋር ተያይዘው የሚነሱ አንዳንድ ጥያቄዎች

በአድማሱ ገበየሁ
ኅዳር 2000 ዓ.ም
ስቶኮልም፣ ስዊድን

በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተለያዩ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ጋር እንወያያለን። በርካታ ጥያቄዎችም ያቀርቡልኛል። ከነዚህም ውስጥ ሌሎችም ቢያውቋቸው ይበጃል የምላቸውን ጥቂት ጥያቄዎችና መልሶች አቀርባለሁ።

1. **በቅንጅት ማኒፌስቶ ውስጥ የስምምነት (ኮንሰንሰስ) ዲሞክራሲ፣ የሊበራል ዴሞክራሲና የሶሻል ዴሞክራሲ ቅንጅት የሚከተላቸው አቅጣጫዎች እንደሆኑ ተጠቅሷል። እነዚህ ሦስቱን እንዴት ማያያዝ (ማስማማት) ይቻላል?**

ቅንጅት በምርጫ ማኒፌስቶው መግቢያ ላይ እንዳሠፈረው፡ « ... **በአገራችን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች ሁሉ ስለአገራችን የሚያሰሙት ድምፅ እንዲደመጥ የሚረዳ የስምምነት (ኮንሰንሰስ) ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዲኖር መታገል ነው።**»

በተጨማሪም «**በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ መግባባት በኢትዮጵያ እእንዲፈጠር ማድረግ ከስምምነት (ከኮነሰንሰስ) ዴሞክራሲ እሴቶች መካካል ዋነኛው ነው።**» ይላል የቅንጅት ማኒፌስቶ።

ኢትዮጵያችን - በርካታ የተለያዩ አኗኗር፣ የተለያዩ ኃይማኖቶች፣ የተለያዩ ፖለቲካዊ አምነቶች፣ ወዘተ. ያላቸው ሕብረተሰቦች የሚኖርባት አገር ናት። በመሆኑም ልዩነቶችን ለማቻቻልና ለማጥበብ፣ ብሎም በአኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ለመፍጠርና የጋራ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚቻለው **የስምምንት (ኮንሰንሰስ) ዴሞክራሲ አሠራርን (ሞደልን)** በሥራ ላይ በማዋል ነው።» የቅንጅት አቋም ይህ ነው።

«**ቅንጅት የማንኛውም የኢትዮጵያዊ ግለሰብ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ሙሉ በሙሉ የሚከበርበት ሕብረ-ብሔራዊ ሕብረተሰብ እንዲያብብ ይታገላል። እጅግ ውብ የሆነው የሰው ልጅ እሴት ነፃነት እንደመሆኑ በሁሉም መስክ የግለሰብ ነፃነት ቀዳሚ ሥፍራ ይይዛል።**» ይህ ዓይነት አስተሳሰብ **የሊበራል ዴሞክራሲ** መሠረት ነው።

ቅንጅት በማኒፌስቶው ውስጥ፣ ሁሉም አካባቢዎች የተቀራረበ ደረጃ ያላቸው የትምህርት፣ የጤና፣ የመገናኛ መስመሮች፣ ወዘተ. እንዲኖሯቸው ማድረግ፤ በተጨማሪም በአካል ጉዳተኝነት፣ በእርጅና፣ በወላጅ እጦት፣ ወዘተ. ምክኒያት ድጋፍ የሚያስገልጋቸውን ዜጎች መንከባከብ ያስፈልጋል በማለት «**በዚህ መንገድ ማኅበራዊ ፍትሕ እንዲረጋገጥ ማድረግ ከሶሻል ዲሞክራሲ ጠቃሚ እሴቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው።**» በማለት ስለሾሳል ዲሞክራሲ ያለውን አቋሙን ግልፅ አድርጓል።

የስምምነት (ኮንሰንሰስ) ዲሞክራሲ ሞደል ለንፅፅር የሚቀርበው ከአብላጫ (ማጆሪታሪያን) ዲሞክራሲ ሞዴል ጋር ነው። የሁለቱን የዲሞክራሲ ሞደሎች በአስር ዘርፎች በመከፋፈል የቀረበ ንፅፅር በሰንጠረዥ 1 ውስጥ ማየት ይቻላል። የስምምነት ዴሞክራሲ ሞደልን በርካታ የአውሮፓ አገሮች በተሟላ መልኩም ይሁን በከፊል በሥራ ላይ አውለውታል። እንደዚሁም የአብላጫ (ማጆሪታሪያን) ዲሞክራሲ ሞደል የሚባለው ደግሞ በእንግሊዝና በሌሎችም አገሮች በሥራ ላይ ውሏል።

**2. *ቅንጅት የሴቶችን በምክር ቤት አባልነት ድርሻ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ በብሔራዊ፣ በክልል፣ በወረዳ፣ እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ አሁን ካለበት 10 በመቶ ገደማ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ ይቻላል ብሎ በማኒፌስቶው ውስጥ አስፍሯል፡፡ ይህ እንዴት ሊሳካ ይችላል?***

በቅንጅት ማኒፌስቶ እንደተጠቀሰው ቅንጅት ሥልጣን ቢይዝ፣ «በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በሚደረግ ጥረት ከአስር ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ:- በተወካዮች (በብሔራዊ) ምክር ቤት አሁን ካሳቸው 7.7 ከመቶ ድርሻ ወደ 50 ከመቶ፣ - በክልል ምክር ቤቶች አሁን ካሳቸው 11.4 ከመቶ ድርሻ ወደ 50 ከመቶ፣ በወረዳ ምክር ቤቶች አሁን ካሳቸው 7.0 ከመቶ ድርሻ ወደ 50 ከመቶ፣ በቀበሌ ምክር ቤቶች አሁን ካሳቸው 14.0 ከመቶ ድርሻ ወደ 50 ከመቶ፣ ከፍ እእንዲል የሚያስችሉ ሁለገብ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ፡፡ ለእዚህ ዕቅድ ተግባራዊነት የሚረዳ የምርጫ ሥርዓትና የሕግ መሠረት እንዲኖርም ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡» ነው የሚለው፡፡

በተጨማሪም «በመንግሥት ሥራ ውስጥ በውሣኔ ሰጭነት የኃላፊነት ቦታ ላይ አሁን ያሳቸው 2 ከመቶ ተሳትፎ ወደ 20 ከመቶ እንዲያድግ ለማድረግ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ ይካሄዳል፡፡» ነው የሚለው፡፡

በሕገ መንግሥቱ መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል የተደነገገው የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ሥርዓት ነው፡፡ ከሁሉ በፊት፣ ይህ የምርጫ ሥርዓት **በተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት** መተካት አለበት ብሎ ቅንጅት ያምናል፡፡

ተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ተመራጭ የሚሆነው አንድ ብቻ ሳይሆን በርካታ ይሆናሉ፡፡ ለውድድር የሚቀርቡት ግለሰቦች ሳይሆኑ ፓርቲዎች ይሆናሉ፡፡ ይህንን አማራጭ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተግባር የተቀበለው መሆኑን ባለፈው ምርጫ ግለሰቦችን ሳይሆን ፓርቲዎችን በመምረጥ አሳይቷል፡፡

የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ክልል አከላለል አንድ አማራጭ በሰንጠረዥ 2 ቀርቧል፡፡ በዚህ አማራጭ መሠረት በየምርጫ ክልሉ የተመደበው የመቀመጫ ብዛት በአገር ደረጃ በአማካይ 10 ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ ያሉት 23 የምርጫ ክልሎች (ወረዳዎች) ተጠቃለው አዲስ አበባ የድርሻውን 23 ተወካዮቹን የሚያስመርጠው ከዚሁ ከአንዱ የምርጫ ክልል መሆን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ፓርቲ ቁጥራቸው እስከ 23 የሚደርሱ ተወዳዳሪዎችን በእለፍ ተቀደም ዘርዝሮ ያቀርባል፡፡ መራጩ ሕዝብ ድምፁን ለየፓርቲዎች ከሰጠ በኋላ እነዚህን 23 መቀመጫዎች ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በአጠቃላይ ካገኙት ድምፅ ጋር በተመጣጠነ መልኩ ይከፋፈሉታል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ፓርቲ ከ23 መቀመጫዎች ውስጥ አሥሩን ቢያሸንፍ፣ ዘርዝሮ ካቀረባቸው እጩዎቹ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አሥሩ ያልፋሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ የምርጫ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ዝጉርጉር (ወይም ዜብራ) የሚባለውን ዓይነት ዝርዝር አቀራረብን ሥራ ላይ በማዋል የሴቶችና የወንዶች የምክር ቤት መቀመጫዎች ድርሻ እኩል እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ አማራጭ ውጤታማ የሚሆነው በሕግ ተደንግጎ በሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገ ብቻ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አማራጭ በሥራ ላይ ከዋለ ደግሞ ቀደም ብሎ በቀረበው ምሳሌ ውስጥ ከተመረጡለት አሥሩ ውስጥ አምስቱ ሴቶች፣ አምስቱ ደግሞ ወንዶች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ቅንጅትም የሚታገለው ይህ ዓይነት የምርጫ ሥርዓት በሥራ ላይ እንዲውል ነው፡፡

### 3. የቅንጅት አርማ ፀሐይ፣ የምርጫ ምልክት ደግሞ ጣቶች መሆናቸው ይታወቃል:: ትርጓሜያቸው ምንድነው?

ፀሐይ የቅንጅት አርማ ናት:: ጨለማ የጥላቻ፣ የጭንቀት፣ የድንቁርና ምልክት እንደሆነ ሁሉ በአንፃሩ ደግሞ ብርሃን የፍቅር፣ የተስፋ፣ የእውቀት ምልክት ነው:: ቅንጅት ነፃነት፣ ፍትሕና ሰላም ለሁሉም ዜጋ ልክ እንደ ፀሐይ ሙቀትና ብርሃን በሁሉም አቅጣጫ እኩል በሆነ መልኩ እንዲሰራጭና እንዲዳረስ ያለውን ፍላጎት ያመለክታል::

ሁለቱ ጣቶች የድልና የሰላም ምልክት ናቸው:: የቅንጅት የምርጫ ምልክት የሆነው ሁለት ጣቶችን ዘርግቶ ሌሎችን ሦስት ጣቶች በማጠፍ ማሳየት ትርጉሙ ድልና ሰላምን አጣምሮ የያዘ ነው:: ድል የሚባለው ማን ማንን ሲያሸንፍ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: በቅንጅት እምነት መለያየትን - አንድነት፣ ጥላቻን - ፍቅር፣ ግፍን - ፍትሕ፣ ድህነትን - ብልጽግና፣ ድንቁርናን - እውቀት፣ በሽታን - ጤና፣ ወዘተ. ሲያሸንፉ ነው ድል የሚባለው:: በዚህ ድል ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል እንጂ ሰላም የሚያጣ ወገን የለም:: የሰላም መለኪያ ምልክት የእያንዳንዱ ዜጋ ሁኔታ ነው:: እያንዳንዳንዱ ዜጋ ውስጥ ሰላም ከሌለ በድምሩ አገራችን የተረጋጋ ዘላቂ ሰላም ሊኖራት አይችልም:: የቅንጅት የድልና የሰላም ምልክት ትርጉሙ ይህ ነው::

### 4. ቅንጅት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚጠቀምበት አደረጃጀትና አሠራር ምን ይመስላል? ቅንጅት አሁን ካለው የበለጠ እንዲጠናከርስ ምን ቢያደረግ ይሻላል?

ቅንጅት ሁለት ወሳኝ እርከኖች አሉት:: እነሱም የፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔና የየወረዳው ያሉ የፓርቲው አባሎች ናቸው::

ጠቅላላ ጉባዔው ከፍተኛው የፓርቲው የሥልጣል አካል ነው:: የጠቅላላ ጉባዔ አባሎች በዋነኛነት የየወረዳው ተወካዮች ናቸው:: ጠቅላላ ጉባዔው የማዕከላዊ/ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን በምርጫ ይሰይማል:: ማዕከላዊ ምክር ቤትም በበኩሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን (ከአባሎቹ ውስጥ) መርጦ ይሰይማል::

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሁሉም የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ ወረዳ ነው:: ለተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ)፣ ለክልል ምክር ቤት፣ ለዞን ምክር ቤት (ለአንዳንድ አካባቢዎች) እና ለወረዳ ምክር ቤት መሠረት የሆነው የምርጫ ክልል ወረዳ ነው:: (የተወካዮች ምክቤትን መቀመጫ ብዛትና የየክልሎች ምክር ቤቶችን መቀመጫዎች ብዛት በሰንጠረዥ 3 ይመልከቱ::) በመሆኑም የየወረዳ የፓርቲ አካሎች ለሕዝብ ቅርብ በመሆናቸው ወሳኙን የቅንጅት እርከን ይይዛሉ:: የወረዳ አካሎች በአኪልነት ደረጃ ጀምረው እስከ ምክር ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ:: የየወረዳ የፓርቲ አካሎች በዋነኛነት የሚንቀሳቀሱት በየወረዳው በሚኖሩ አባሎች ነው::

የወረዳ ምክር ቤትን ለማቋቋም መጀመሪያ አስኳል መፍጠር ያስፈልጋል:: እጅግ ወሳኙ ሥራ ለየወረዳው አስኳል የሚሆኑ ቡድኖች ማደራጀት ነው:: አባላትን መመልመል የተወሰኑ የሥራ ዘርፎች ብቻ ሥራ ኤደለም:: በየወረዳው አባላትን ለመመልመል ምን መደረግ አለበት? በዋነኛነት ምን ዓይነት ዘዴ መጠቀም ያዋጣል? በየወረዳው ምክር ቤት ተቋቁሞ የተመደበለትን ሥልጣን ተረክቦ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እስኪያደርግ ድረስ የሽግግሩ ሁኔታ እንዴት ይስተናገዳል? የመሳሰሉት ጥያቄዎች አግባብነት ያለው መልስ መልስ ማግኘት አለባቸው::

ቅንጅት ባለፈው በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ በየአካባቢው ኢጅግ ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ማግኘቱ ይታወቃል:: በተለይም በአዲስ አበባ፣ በሌሎች በርካታ ሕዝብ በሚኖርባቸው ከተሞችና በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተገኘው ውጤት በኢሕአዲግም ቢሆን ሊሸፈጥ አልተቻለም:: ይህን መገንዘብ ቅንጅት ወደፊት ለሚያደርገው ድርጅትን የማጠናከር ሂደት ወሳኝነት አለው:: በየከተማው የሚኖሩ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም በየከፍተኛ ትምህርት ቤት ተቋማት የሚገኙ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች በየወረዳው የተፈጠሩ አስኳሎች እንዲጠናከሩና እንዲሁም  አስከአሁን ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች አዳዲስ አስኳሎች እንዲፈጠሩ በሚደረገው ጥረት የየበኩላቸውን እገዛ የሚያደርጉበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል:: በየከፍተኛ ከተሞችም ሆነ በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች በየወረዳዎች ያሉትን ነባር አስኳሎችን የማጠናከርም ሆነ አዳድስ አስኳሎችን የመፍጠር ሥራ በተቀላጠ አሠራርና በአጭር ጊዜ እንዲሳካ ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው::

ቅንጅት ከምክር ቤቶች በተጨማሪ የእለት ከእለት ሥራዎችን የሚያከናውንበት  ጽሕፈት ቤቶች አሉት:: ግን ገና በርካታ ተጨማሪ ጽሕፈት ቤቶች ያስፈልጉታል::

በአዲስ አበባ ከተማ የተከፈተ ዋና (ማዕከላዊ) ጽሕፈት፣ አዲስ አበባን ጨምሮ በየአካባቢው ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለማስተባበር የሚያገለግሉ በየአቅጣጫው አመቺ በሆኑ ከተሞች የተከፈቱ ጽሕፈት ቤቶች ነበሩት:: የተዘጉትን መክፈት ቅድሚያ ሥራ ይሆናል:: ያም ሆነ ግን ገና በርካታ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቶች ያስፈልጉታል:: (ጽሕፈት ቤት ያስፈልጓቸውን ተብሎ በአማራጭነት የቀረቡትን አካባቢዎች ዝርዝር በሰንጠረዥ 4 ይመልከቱ::) በተጨማሪም የወረዳ አባሎች ተጠናክረው የወረዳ ምክር ቤት ማቋቋም በሚችሉበት አከባቢ ሁሉ በራሳቸው ጥረት የራሳቸውን ሥራ የሚያስፈጽም ጽሕፈት ቤት እንዲከፍቱ መበረታታት አለባቸው::

5. አንዳንድ የቅንጅት አባሎችና ደጋፊዎች ውሕዴቱ እንቅፋት እያጋጠመው ነውና የሚሻለው ውሕዴት የፈጠሩት ፓርቲዎች በፊት ወደነበሩበት ተመልሰው የየራሳቸውን ሕልውና ቢያስጠብቁ ይሻላል ይላሉ:: ይህ አስተሳሰብ ልክ ነው?

እስቲ አንድ ሂሳባዊ ጥያቄ እናንሳ:- መኢአድ ሲደመር ኢዴአፓ-መድኅን ሲደመር ኢዲሊ ሲደመር ቀስተ-ደመና ውጤቱ ምን ይሆናል:: ከቅንጅት ይበልጣል? ከቅንጅት ጋር እኩል ይሆናል? ከቅንጅት ያንሳል? ይህንን ጥያቄ ሁላችንም ለመመለስ ስንሞክር ለመልሳችን ምክኒያቶቻችንን እናቅርብ::

| | | |
|---|---|---|
| **መኢአድ + ኢዴአፓ-መድኅን + ኢዲሊ + ቀስተ-ደመና** | **?** | **ቅንጅት** |

በበርካታ ሰዎች እምነት ቅንጅት ውሕደቱን ከፈጠሩት አራት ድርጅቶች ድምር እጅግ የላቀ ነው:: ቅንጅት በመፈጠሩ በአንድ አፍታ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ማግኜት ተችሏል:: ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑት ውስጥ አንዱ የሚያዚያ 30 ቀኑ በአዲስ አበባ ሕዝብ የተሠራው ታምር ነው:: በአጠቃላይ ቅንጅት ባይፈጠር ኖሮ ከዚያ ሁሉ በየአከባቢው ከተገኘው ከፍተኛ ውጤት ውስጥ ሲሦውን እንኳን ማግኜት አይቻልም ነበር:: ቅንጅት ባይኖር የእርስ በርስ መጠላለፍ ይስከትና ውጤታማ የሆነ የሕዝብን ድጋፍ ማግኜት አይቻልም ነበር::

ሁለተኛው ጥያቄ ከውሕዴቱ በኋላ እንደገና ውህዴት የፈጠሩትን ድርጅቶች መልሶ በነበሩበት ሁኔታ መልሶ ማቋቋም ይቻላልወይ? ይህንንም ጥያቄ ሁላችንም ለመመለስ እንሞክር::

ቅንጅትን የፈጠሩት አራቱ ፓርቲዎች የጋራ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያስገኝ ጥንካሬ ለማግኘት ሲሉ በመዋሃዳቸው ለአባሎች፣ ለደጋፊዎችና በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ተስፋን ፈንጥቀዋል:: በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ውሕደቱ የፈጠረው ውስጣዊ ችግር አለ የሚል ስሞታ አለ:: የውስጥ ችግር ከውህደት በፊት ፓርቲዎች ለየብቻቸው ይንቀሳቀሱ በነበሩበት ጊዜም ነበረ ከውሕደት በኂላም አለ፣ ወደፊትም ይኖራል:: መፍትሔው ግን የችግሮችን መፍትሄ በትዕግሥት በመመካከር ፈልጎ ማግኘትና ተግባራዊ ማድረግ እንጂ ሰበብ እያበዙ ቢሸሹት ያባርራል እንጂ አይመለስም::

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት አንድ ጉዳይ አለ:: እርግጥ ነው አራት ፓርቲዎች ሲዋሃዱ የሚኖራቸው አራት ሊቀመንበር ሳይሆን አንድ ሊቀመንበር ነው:: በየደረጃው በርካታ ወንበሮች ስለሚታጠፉ መሸጋሸግ ይኖራል:: ይህን እውነታ ሰበብ ሳያበዙ መቀበል ያስፈልጋል::

ቅንጅትን ወደ አባል ድርጅቶች ፈጽሞ መመለስ አይቻልም:: በምርጫው ሂደትና ከዚያም በኂላ መስከረም 14 ቀን 1998 በተደረገው የውህደት ስምምነት መሠረት ቅንጅትን በፈጠሩት አራት ፓርቲዎች ውስጥ የነበሩ አባሎች ተደባልቀዋል:: በፊት ይታይ የነበረው መናቆር እጅግ በጣም ቀንሷል:: አባሎች ዓላማቸው አንድ በመሆኑና በምርጫው ሂደት በተፈጠረው የትግል መድረክ አብረው በመሥማራታቸው ተቀራርበዋል፣ተግባብተዋል:: ይህን የእድገት ደረጃ መቀልበስ ፈጽሞ አይቻልም:: ወደ ዱሮው ሁኔታ እመለሳለሁ የሚል ቢኖር ትርፉ ኪሣራ ብቻ ነው:: ምናልባት ስምን መመለስ ይቻል ይሆናል እንጂ በርካታ የአመራር አባላትን፣ እጅግ በርካታ አባላትንና ደጋፊዎችን መልሶ ወደ ድሮው ቦታ መመለስ የሚቻል አይደለም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ልብ ያለው ልብ ይበል ከማለት ውጭ ብዙ መጨመር አያስፈልግም::

## 6. በቅንጅት አባሎችና ደጋፊዎች መከከል የጠበቀ የትግል ቤተሰብነት ትስስር መንፈስ እንዲዳብር ምን መደረግ አለበት? ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ቁምነገሮች ምን ምን ናቸው?

በአባሎች መካከል ጤነኛ ግንኙነት እዲኖር ከተፈለገ የድርጅት ዲስፐሊን መጠበቅ፣ በአመራርና በሌላ ደረጃ ባሉ አባሎች መካከል የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ መኖር፣ የአመራርና በሌላ ደረጃ ያሉ አባሎች አንድነት፣ ውስጣዊ ቅራኔን በአግባቡ መያዝ፣ ፓለቲካዊ ግንዛቤ (ብስለት) እአንዲያድግ መጣር፣ እና የመሳሰሉት ዋና ዋና ጉዳዮች (አቅም በፈቀደ መጠን) ትኩረት ማግኘት አለባቸው::

የድርጅት ዲስፐሊን በማንኛውም አባል **መጠበቅ** አለበት:: ድርጅታዊ ዲስፐሊን መጠበቅ ማለት የድርጅቱ ፖለቲከ ፕሮግራምና የድርጅቱ የአሠራር ደንብና ሥርዓት በሁሉም አባሎች መከበር አለበት:: በተለይም የአመራር አባላት ሁሉ ይህንኑ የማክበርና የማስከበር ቀዳሚ ኃላፊነት እንዳለባቸው ለአፍታም ሊዘነጉት አይገባም:: አባሎች ሁሉ የድርጅቱን ውሳኔ በታማኝነት መፈፀምና ማስፈፀም አለባቸው:: ሁሉም ጉድለት የማረም ሂደት በቅን ልቦናና በመማማር መንፈስ መከናወን አለበት:: አንዱ ሌላውን ማኮሰስም ሆነ ከመጠን በላይ መከብ የለበትም:: በመሸፋፈንም ሆነ በመዘራጠጥ ድርጅትን ማሳደግ አይቻልም፣ ትናንት የጣሉትን ዛሬ ከመጠን በላይ ማወደስ ወይም ትናንት ያሞገሱትን ዛሬ ማጣጣል ሚዛናዊ አሠራር ሊሆን አይችልም:: በርከታ ቁምነገሮችን ያከናወነ አባል ስህተት ቢሠራ በፈፀመው ስህተት ይወቀሳል ወይም ይጠየቃል እንጂ በፊት ያደረገው በጎ አስተዋጽኦ ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ ባዶ መቅረት የለበትም::

በአመራርና በሌላ ደረጃ ባሉ አባሎች መካከል የተጠናከረ **የመረጃ ልውውጥ** መኖር አለበት:: መሪዎች ስለ ድርጅቱ ያለፈ፣ የአሁንና የወደፊት እንቅስቃሴ ለአባሎች በየወቅቱ

ግልፅ በሆነ መንገድ መረጃ መስጠት አለባቸው:: በተቻለ መጠን አባሎችና መሪዎች በግልፅ የሚወያዩበት መድረክ መፈጠር አለበት:: በቂ የሃሳብና የመረጃ ልውውጥ ካልተደረገ ለድርጅቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በቂ አቅም መፍጠር አይቻልም::

የአመራርና በሌላ ደረጃ ያሉ አባሎች አንድነት ለፓርቲ እእንቅስቃሴ መሳካት ወሳኝ ነው:: በመሠረቱ ሁሉም የድርጅቱ አባሎች የአመራር ችሎታ እእንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ ከአባላት መካከል መርጦ ድርጅቱን እንዲመሩት መሾም ደግሞ የግድ አስፈላጊ ነው:: የተመረጡት የአመራር አባሎች በድርጅቱ ውስጥ ለሚፈለገው የጠበቀ አንድነት ምልክቶች መሆናቸው መዘንጋት የለበትም:: ተመራጭ መሪዎችም ይህንን አደራ በአግባቡ ለመወጣት ሌት ተቀን ሳይዘናጉ በትጋት መሥራት ይኖርባቸዋል:: እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ቁም ነገር ለመሪዎች የሚገባው ከበሬታ ከተመሪዎች ዝም ብሎ የሚሰጥ ሳይሆን መሪዎቹ ራሳቸው እንደየሥራቸውና እኢንደጥረታቸው የሚያገኙት መሆኑ ነው:: *"Respect to leadership is not given, but must be earned."* ይባላል::

ውስጣዊ ቅራኔን በአግባቡ መያዝ ድርጅትን ለማጠናከር ወሳኝነት አለው:: በፓርቲው ውስጥ ግልፅ የሆነ የክርክርና የውይይት ባህል እንዲያድግ ጥረት መደረግ አለበት:: መሪዎች ከመተቸት ነፃ ሊሆኑ አይገባም:: በተቻለ መጠን በየደረጃው ያሉ አባሎች የሚያቀርቡትን ሃሳብና አስተያየት ማዳመጥና መከታተል ይኖርባቸዋል:: እያንዳንዱ አባል ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለመፈፀም የሚያስችል ብቃት እንዲኖረው የድርጅቱን ፕሮግራምና የአሠራር ደንብ ማወቅ ይጠበቅበታል:: እንዳንዱ አባል በየጊዜው ተሳትፎውን ማሳደግ ይኖርበታል:: የአባላት እርስ በእርስ ግልፅና መከባበር በተመላበት መንገድ መተቻቸት ለድርጅቱ እድገትን ያስገኛል::

ፖለቲካዊ ግንዛቤ (ብስለት) እአንዲያድግ የማቋርጥ ጥረት ማካሄድ ተገቢ ነው:: በመሠረቱ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች ፖለቲካዊ ብስለት (ግንዛቤ) እኩል አይሆንም - እኩል አያድግምም:: በተቻለ መጠን ተያይዞ ለማደግ እንዲቻል ለአቅም ግንባታ በሚበጅ መልኩ አንዱ ለሌላው ጠቃሚ ልምዱንና ግንዛቤውን ለሌሎች ማካፈል ይኖርበታል::

## 7. ቅንጅት አሁን ናለበት የበለጠ እንዲጠናከር በውጭ አገር የሚኖሩ አባሎችና ደጋፊዎች ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

ቅንጅት አሁን ካለው የበለጠ እንዲጠናከር በውጭ አገር የሚኖሩ አባሎችና ደጋፊዎች ገንዘብ በማሰባሰብ፣ የሜዲያ አግልጎት በማደራጀትና በዲፕሎሚሲው መስክ በመሳሰሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት የተጣለባቸውን አደራ መወጣት ይጠበቅባቸዋል::

በየደረጃው ያሉ ጽሕፈት ቤቶች ተጠናክረው ሥራቸውን እንዲሠሩ ማነቆ ከሆኑት ችግሮች ዋነኛው ሙሉ ጊዜያቸውን በፓርቲው ሥራ ላይ ሊያውሉ የሚገባቸውን የቋሚ ሠራተኞች ደሞዝ፣ የጽሕፈት ቤት ኪራይ፣ የእንቅስቃሴ ወጪ፣ እና የመሳሰሉትን ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ማግኜት ነው:: ይህ ዓይነቱ ወጪ በውጭ አገር በሚኖሩ አባሎችና ደጋፊዎች ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው መልኩ ቢታገዝ ትልቁ ማነቆ ሊወገድ ይችላል::

ኢሕአዴግ የሕዝብ ንብረት የሆኑትን መገናኛ ብዙሃን (ሜዲያ) ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አውሎ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ አድርጓቸዋል:: ተቀናቃኞች ሃሳባቸውን ለሕዝብ

ያቀርቡባቸው የነበሩት ውስን የነፃ ፕረስ የሕትመት ውጤቶችም ተዳፍነዋል:: በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሃሳብንና መልእክትን ለሕዝብ ማስተላለፍ አልተቻለም::

መረጃ ኃይል ነው:: ቅንጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት እንዲስመዘግብ ካስቻሉት ሁኔታዎች አንዱ መረጃንና ሃሳብን ለማሰራጨት በሚያስችሉ ዘመናዊ ሜዲያዎች ለመጠቀም ትንሽ ጭላንጨል ለማግኘት መቻሉና ያችንም ዕድል በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋሉ ነው:: ቅንጅት በምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ወቅት በጥቂት ደቂቃዎች የሚቆጠሩ የሜዲያ የአየር ጊዜ በማግኘቱ ከኢትዮጵያን ሕዝብ ጋር ልብ ለልብ መናበብ አስችሎታል:: አሁንም፣ ወደፊትም ሜዲያ እጅግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: በመጠኑም ቢሆን በአሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልእክት ማስተላለፍ የሚቻለው በአሜሪካ ድምፅና በጀርመን ድምፅ ሬድዮ ነው:: በእነዚህ ሬድዮ ጣቢዎች አልፎ አልፎ የሚተላለፉትን ጠቃሚ የሆኑ ፕሮግራሞች ደግሞ ለመስማት እንኳን የሚቻልበት ሁኔታ የለም:: የሰማም ሳያጣጥማቸው፣ ያልሰማም ሳይሰማቸው ይቀራል:: በተለይም አካባቢ ሳይወስነው በገጠርም ሆነ በከተማ ለሚኖረው ሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ በመረጃ አቅርቦቱ ታማኝና ሚዛናዊ የሆነ በአጭር ሞገድ የሚሰራጭ የሬድዮ አገልግሎት የማግኜት ጉዳይ ቅድሚያ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል:: በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እንዲህ ዓይነቱን ወሳኝ መሣሪያ አቅማቸውን አቀናጅተው እውን ሊያደርጉት ይገባል:: በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በተባበረ ጥረት የኢትዮጵያን ሕዝብ ዛሬ ነገ ሳይሉ ሚዛናዊ የሆነ ትክክለኛው መረጃ እንዲያገኝ በማድረግ ከኢሕአዲግ አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ ሊገላግሉት ይገባል::

በተጨማሪም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በየሚኖሩበት አካባቢ ባሉት ባለሥልጣናት ላይ ምን ያህል ጫና መፍጠር እንደሚችሉና እነሱም የዚያኑ ያህል በኢሕአዲግ ላይ ጫና መፍጠር እንደሚችሉ በቂ ምስክር የሚሆነው የቅንጅት መሪዎችን ለማስፈታት የተደረገው ትግል ነው:: ይህ ዓይነቱ አሠራር ለተለያዩ አጀንዳዎች በሚያመች መልኩ እተቀየሰ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት:: ይህንን ዓይነት የሕዝብ አደራ በአግባቡ ለመወጣት ደግሞ ከምን ጊዜውም በላይ አንድነትን አጠናክሮ መታገል አስፈላጊ ነው::

የጠቀስኳቸውንና ሌሎችንም አስፈላጊ ተግባራት ከግባቸው ለማድረስ ደግሞ መደራጀት አስፈላጊ ነው:: የተደራጀ ኃይል የተበታተነን አቅም ያሰባስባል፣ ያሰበውን በዕቅድ ይይዛል ከዚያም በተግባር ማዋል ይችላል:: ይህም በጎ ጅማሬ እየታየ ነው፣ በዚሁ መንገድ ከአሁኑ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት::

አሁን በየቦታው ያሉ በምርጫ የተሠየሙ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ማኅበራት አመራሮች በቅንጅት መተዳደሪያ ላይ የተጠቀሰውን (ነገር ግን ገና ያልተቋቋመውን) በመሰለ የአማካሪዎች ምክር ቤት ቢታገዙ የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ አማካሪዎች ከአሁን ቀደም በተመሳሳይ ሥራ ላይ ሲሳተፉ የነበሩ እና በተለያየ ምክኒያት በአመራር ቦታ ላይ ሊሳተፉ የማይችሉ ነገር ግን ለአካባቢያቸው የድጋፍ ማኅበር የምክር አስተዋጽኦ ለማበርከት እውቀቱና ልምዱ ያላቸው ቢሆኑ መልካም ነው:: ይህ ዓይነቱ የአማካሪዎች ምክር ቤት በአባላት መካከል ቅሬታ በሚፈጠርበትም ጊዜም እንዳስፈላጊነቱ የአስታራቂነት ሚና ሊጫዎት ይችላል::

## ሰንጠረዥ 1፡

**የአብላጫን (Majoritarian) ዴሞክራሲ ሞደልንና የስምምነት (Consensus) ዲሞክራሲ ሞደልን አረንድ ሊፋርት[1] የተባለ ምሁር በአስር ዘርፎች በመከፋፈል በሚከተለው መልክ በንፅፅር አቅርበውታል፡፡**

| ቁ. | ተቋማዊ ሁኔታ | የአብላጫ ሞዴል | የስምምነት (የኮነሰንሰስ) ሞዴል |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥራ አስፈፃሚነት ሥልጣን | የአስፈፃሚው ሥልጣን ከአንድ አሸናፊ ፓርቲ በሚመደብ ግለሰብ ላይ የተከማቸ ነው፡፡ | የአስፈፃሚው ሥልጣን የተለያዩ ፓርቲ አባሎችን በሠፊ ጥምረት ያካተተ ነው፡፡ |
| 2 | በአስፈፃሚና በሕግ አውጪ መካከል ያለው ሁኔታ | ሥራ አስፈፃሚው በሕግ አውጪው ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡ | በሥራ አስፈፃሚና በሕግ አውጪ መካከል የተመጣጠነ ሥልጣን ይኖራል፡፡ |
| 3 | የፓርቲዎች ሥርዓት | የሁለት ፓርቲዎች (ብቻ) እየተቀያየሩ ሥልጣን ይይዛሉ፡፡ | በርካታ ፓርቲዎች እንደየድጋፋቸው መጠን ሥልጣን ይጋራሉ፡፡ |
| 4 | የምርጫ ሥርዓት | የአብላጫና ያልተመጣጠነ የምርጫ ሥርዓት ይከተላል፡፡ | የተመጣጠነ የምርጫ ሥርዓት ይከተላል፡፡ |
| 5 | ጥቅም አስጠባቂ ቡድኖች (ማኅበራት) | ጥቅም አስጠባቂ ቡድኖች (ማኅበራት) በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲደራጁና ተጠናክረው በፖለቲካው አካሄድ ላይ ጫና እንዲፈጥሩ አይበረታቱም፡፡ | ጥቅም አስጠባቂ ቡድኖች (ማኅበራት) በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲደራጁና ተጠናክረው በፖለቲካው አካሄድ ላይ ጫና እንዲፈጥሩ ይበረታታሉ፡፡ |
| 6 | ብሔራዊ ባንክ | ብሔራዊ ባንክ በአስፈፃሚው ቁጥጥር ሥር ነው፡፡ | ብሔራዊ ባንክ ከአስፈፃሚው ቁጥጥር ውጭ ነው፡፡ |
| 7 | የመንግሥት ዓይነት | አሃዳዊ የሆነ (ያልተማከለ) አስተዳደርን ይከተላል፡፡ | ፌደራላዊ አወቃቀርንና በየደረጃውና በየአከባቢው የተጠናከረ አስተዳደር መፈጠርን ይከተላል፡፡ |
| 8 | ሕግ አውጭ አካላት | አንድ የሕግ አውጭ ምክር ቤት ብቻ ይቋቋማል፡፡ | አንድ የተወካዮች ምክር ቤትና አንድ የፌደሬሽን ምክር ቤት ይቋቋማሉ፡፡ |
| 9 | ሕገ መንግሥት | ሕገ-መንግሥትን በቀላሉ መከለስ ይቻላል፡፡ | ሕገ-መንግሥትን በቀላሉ መከለስ አይቻልም፡፡ |
| 10 | የሕገ ምንግሥት ትርጓሜ | የአገሪቱ ፓርላማ ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን አለው፡፡ | ሕገ መንግሥትን የመተርጎም ሥልጣን የሕገ ምንግሥት ተርጓሚ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው፡፡ |

1. *አረንድ ሊፋርት* (***Arend Lijphart***) *በዓለማችን ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለበርካታ ዓመታት በማስፈን በኩል ተሳክቶላቸዋል የሚባሉ አገሮችን በማነፃፀር ያስተዋሉትን ጥልቀት ያለው ግኝት አርበዋል፡፡ የአብላጫን ዴሞክራሲና የስምምነት (የኮንሰንሰስ) ደሞክራሲ ሞደሎችን መሠረታዊ ልዩነቶች በግልፅ ማሳየት ችለዋል፡፡*

## ሰንጠረዥ 2፡

*የተመጣጣኝ ውክልና ምርጫ ሥርዓት የምርጫ ክልል አከላለል ምን ሊመስል እንደሚችል ለማሳየት ያህል ለተወካዮች ምክር ቤት የሚያገለግል አንድ አማራጭ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ይህ አማራጭ በአብዛኛው ከዞኖች ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡*

| ተ.ቁ | ክልል | የዞኖች ብዛት | የምርጫ ክልል ብዛት | የመቀመጫ ብዛት | ለየምርጫ ክልሎች የሚደርስ አማካይ የመቀመጫ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | - | 1 | 23 | 23 |
| 2 | ኦሮሚያ | 12 | 12 | 178 | 15 |
| 3 | አማራ | 10 | 10 | 138 | 14 |
| 4 | ደቡብ ብ.ብ.ሕ | 10 | 10 | 123 | 12 |
| 5 | ትግራይ | 4 | 4 | 38 | 10 |
| 6 | ሶማሌ | 8 | 8 | 23 | 3 |
| 7 | አፋር | 5 | 3 | 8 | 3 |
| 8 | ቤኒሻንጉል - ጉሙዝ | 3 | 3 | 9 | 3 |
| 9 | ጋምቤላ | 4 | 1 | 3 | 3 |
| 10 | ድሬደዋ | - | 1 | 2 | 2 |
| 11 | ሐረሪ | - | 1 | 2 | 2 |
| ጠቅለላ ድምር | | | 54 | 547 | 10 |

## ሰንጠረዥ 3፡

*ክልሎች በተወካዮች ምክር ቤት ያላቸው የመቀመጫ ድርሻና የየክልሉ ምክር ቤት የቀመጫ ብዛት እንደሚከተለው ነው፡፡*

| ተ.ቁ | ክልል | የሕዝብ ብዛት | የተወካዮች ም/ቤት የመቀመጫ ብዛት | የክልል ምክር ቤት መቀመጫ ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 3050000 | 23 | 138 |
| 2 | ኦሮሚያ | 27304000 | 178 | 537 |
| 3 | አማራ | 19624000 | 138 | 294 |
| 4 | ደቡብ ብ.ብ.ሕ | 15321000 | 123 | 348 |
| 5 | ትግራይ | 4449000 | 38 | 152 |
| 6 | ሶማሌ | 4444000 | 23 | 147 |
| 7 | አፋር | 1418000 | 8 | 87 |
| 8 | ቤኒሻንጉል - ጉሙዝ | 640000 | 9 | 99 |
| 9 | ጋምቤላ | 263000 | 3 | 82 |
| 10 | ድሬደዋ | 412000 | 2 | - |
| 11 | ሐረሪ | 203000 | 2 | 36 |
| ጠቅለላ ድምር | | 77127000 | 547 | 1920 |

<u>ማሳሰቢያ</u>፡ የክልሎች የሕዝብ ብዛት በሐምሌ 1999 ዓ.ም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ የተወሰደ ግምት ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 4፡

**አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ከዋናው ጽሕፈት ቤት ሌላ የየአካባቢውን የፓርቲ ሥራ የሚያስተባብሩ የቅንጅት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች - የተከፈቱም እንዲጠናከሩ፣ አዳዲስም እንዲከፈቱ ያስፈልጋል። አቅም በፈቀደ መጠን በቅድሚያ በሚከተለው ሰንጠዥ ውስጥ በተዘረዘሩት ከተሞች ቢከፈቱ የተሻለ አማራጭ ይሆናል የሚል ሃሳብ ቀርቧል።**

| ተ.ቁ | ከተማ | የሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 3059000 |
| 2 | ናዝሬት | 239600 |
| 3 | አሰሳ | 85700 |
| 4 | ጎባ እና ሮቤ | 93400 |
| 5 | ነገሌ | 45000 |
| 6 | አሰበ ተፈሪ | 35000 |
| 7 | ሐረር | 127000 |
| 8 | ድሬደዋ | 293200 |
| 9 | ጊምቢ | 38400 |
| 10 | ነቀምቴ | 88500 |
| 11 | መቱ እና ጎሬ | 50000 |
| 12 | ጅማ | 166600 |
| 13 | አምቦ | 51800 |
| 14 | ፍቼ | 39700 |
| 15 | ወልቂጤ እና ወሊሶ | 77000 |
| 16 | ሆሳዕና | 60200 |
| 17 | አዋሳና ሻሸመኔ | 229000 |
| 18 | ዲላ | 64000 |
| 19 | ሶዶ | 68900 |
| 20 | አርባ ምንጭ | 76000 |

| ተ. ቁ | ከተማ | የሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|
| 21 | ጂንካ | 23600 |
| 22 | ቴፒ/ ቦንጋ | 20200 |
| 23 | ሚዛን | 20200 |
| 24 | ጎንደር | 204000 |
| 25 | ደብረ ታቦር | 40900 |
| 26 | ቻግኒ | 32400 |
| 27 | ባህር ዳር | 175200 |
| 28 | ደብረ ማርቆስ | 89700 |
| 29 | ወልዲያ | 44700 |
| 30 | ደሴ እና ኮምበልቻ | 249100 |
| 31 | ደብረ ብርሃን | 70400 |
| 32 | አድዋ እና አክሱም | 94200 |
| 33 | አዲግራት | 68300 |
| 34 | መቀሌ | 177100 |
| 35 | አሳይታና ዱብቲ | 40000 |
| 36 | ጅጅጋ | 102500 |
| 37 | ጎዴ | 71400 |
| 38 | ጋምቤላ | 32600 |
| 39 | አሶሳ | 20900 |
| 40 | | |

**ማሳሰቢያ፡ የከተሞች የሕዝብ ብዛት በሐምሌ 1999 ዓ.ም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ የተወሰደ ግምት ነው።**